# ዋናተኛው ጃዋር

By Sebat Kilo



ጥቅምት 2002 ዓ.ም፤ ከፍተኛ በራስ መተማመን የሚታይበት የ 23 ዓመት ወጣት ኦሮሞ ብሔረተኛ፤ የኦሮሞ ብሔርተኝነትን የፖለቲካ ንቅናቄ ከዐርባ ዓመታት በላይ የመራውን እና አቅሙ ተዳክሞ ሳይቀር መንፈሳዊ ልዕናውን ያላጣውን የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን በግሩም ቋንቋ እና ባልተለመደ ቀጥተኝነት፣ ያለ ምኅረት እና ያለ ማመንታት በመተቸት ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ራሱን አስተዋወቀ፤ ወጣቱ የድርጅቱን የውስጥ ክፍፍል፣ የአመራር ችግር፣ የፖለቲካ እና የወታደራዊ ድል ማጣት ከደረደረ በኋላ የግንባሩን መሞት አወጀ፤ የኦሮሞ ብሔረተኝነትን ተቋማዊ ንጉሥ አንገቱን ቀላው። ጽሑፉ በኦሮሞ ብሔረተኞች ዘንድ ብቻ ሳይኾን በፓን ኢትዮጵያውያንም ዘንድ ጥዝታ ፈጠረ፤ አንጫጫ። ታዋቂው ፈላስፋ መሳይ ከበደ ለጽሑፉ መልስ ሰጡ። ወጣቱ ጊዜ ሳያባክን ምላሹን ወረወረ። ክርክሩ የኢትዮጵያውያን “ኢንተርኔት” መነጋገሪያ ኾነ፤ የትዊተር አራዶች እንደሚሉት “ኢንተርኔቱን ሰበረው”። ጃዋር ሲራጅ መሐመድ ብጉር ከማውጣቱ በፊት ፖለቲካን ሲያደቅ የኖረ ቢኾንም በዚህ ጽሑፉ እና ከመሳይ ከበደ ጋራ ባደረገው ክርክር ያደባባይ ሰው ኾኖ ተወለደ። ነገር ግን ከዚህም በላይ ጃዋርን ‘ያፈመመው’ ምርጫ 2002 ን በሚመለከት በአልጀዚራ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቱባ ሰውዬ አቶ በረከት ስምዖን በተቃራኒ ኾኖ ባደረገው ክርክር ባሳየው ብቃት ነው። የመንግሥት ደጋፊዎች ሳይቀሩ የ 24 ዓመቱ ጎረምሳ አቶ በረከትን በዝረራ እንደረታ ላለመመስከር አልተቻላቸውም።

ጃዋር መሐመድን ለመጀመርያ ጊዜ የተዋወቅኹት በዚያ ወቅት ነበር። ጃዋር ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በምኖርበት አገር ቋንቋ የአዲሱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ “ገን ስሊንገር” ኾኖ ነበር፤ ትኩስ፣ ፈጣን፣ እንደ ታታሪ ንብ ብዝ ብዝ የሚል እና በየቦታው በሹክሹክታ ጥያቄዎች የሚነሱበትም ነበር። ጠርጣራ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኞች፡- “የዚህ ልጅ ፍላጎት ምንድነው?” ሲሉ . . . . ፓን ኢትዮጵያኒስቶች፡- በተስፋ “ልጁ የኦሮሞ ኦባማ ሊኾን ይችላል?” ሲሉ . . . የኦሮሞ ብሔረተኞች ደግሞ፡- “ጃዋር ከጠላቶቻችን ጋር ብዙ እያመቻመቸ ነውን?” ይሉ ነበር . . . ሁሉም በየቦታው መላምት ይወረውራል። ጃዋርን ብዙ ጊዜ በስልክ እና በግንባር አግኝቼ ተጨዋውተናል። ግን እነዚህ መስተጋብሮች “ጃዋር ጓደኛዬ ነው” ከማለት ያለፈ ስለ ፖለቲካዊ ፍላጎቱ ከተንሾካሿኪዎቹ የተሻለ እውቀት አልሰጠኝም። ይኹንና ይህን እመሰክራለሁ፡- ጃዋር ከሌሎች ዲሲ አካባቢ ከሚንቀሳቀሱ ፖለቲከኞች የተለየ ተክለ ሰብእና ነበረው። ከብዙ ቡድኖች ጋር ለመነጋገር እና ለማድመጥ ዝግጁ ነበር። የኦሮሞ ብሔረተኛ መኾኑ ጥርጥር ባይኖረውም፤ በዚህ አረፋ ውስጥ ራሱን የደፈቀ አልነበረም።

ከዚያ ጃዋር ዲሲን ለቆ መኖሪያውን በሚኔሶታ እና ኒውዮርክ እያፈራረቀ አደረገ። የግራጁዌት ስኩል ፍጋትን እና ጠንካራ የፖለቲካ እንቅስቃሴን አጣመረ። እንደ ብዙ ኢትዮጵያውያን ይኼኛውን ጃዋር

የተከታተልኹት ከሩቅ በሶሻል ሚዲያ ነው። አንዳንድ ማኅበራዊ ሳይንቲስቶች ዲጂታል ዱዋሊዝም የተባለ ሐሳብን ያስተጋባሉ። በዚህ ሐሳብ መሠረት የሰዎች የኦንላይን እና የኦፍላይን ተክለ ሰብእና የተለያየ ሊኾን ይችላል፤ አንዳንዶቻችን በዲጂታል ዓለም ያዙኝ ልቀቁኝ ባይ፤ ሙርጃ ለስላሽ ጽንፈኞች **(abrasive)** ነን፤ ኦፍላይን ባለ መስተጋብር ግን በተቃራኒው ለስላሶች እና አመቻማቾች እንኾናለን። ምሁራኑ ለዚህ ዱዋሊዝም የተለያዩ መንስኤዎችን ያቀርባሉ። መንስዔዎቹ ምንም ይኹኑ ዲጂታል ተክለ ሰብዕናን **"**በክህደት ባይኾንም በጥርጣሬ መመልከት ይበጃል**"** ብዬ በሶሻል ሚዲያ የማየውን ጃዋር በተመለከተ አጠቃላይ የግምገማ ፍርድ ልሰጥ አልቸኮልኩም። ነገር ግን አንድ ነገር ግልጽ ነበር። የሶሻል ሚዲያው ጃዋር ዲሲ በአካል ካገኘኹት ጃዋር በተለየ በራሱ የአይዲዮሎጂ ሰፈር **(ideological enclave)** የከተመ ነው፡፡ ይኼኛውን **"**የሜንጫው**"**ን ጃዋር **"**አወዛጋቢ**"** የሚለው ቃል እንኳን በሚገባ አይገልጸውም። ይኹንና ጃዋር **"**የእነርሱ**"** ብቻ ኾኖ በሌሎች ዘንድ **"**ስምና ዝናው**"** ቢያቆለቁልም የፖለቲካ ጎይሉ **(power)** ግን ጨምሯል። ባለፉት ሦስት ዓመታት በኦሮሞ እና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ የጃዋርን ያህል ጎይለ-ግናኔ ያገኘ የለም፤ የኦሮሞ ፈርስት ንቅናቄ መሪ፣ የጎምቱ የኦሮሞ ኢንቴሌክቹዋል ሕይወት ማዕከል የኦሮሞ ስተዲስ አሶሲዬሽን ፕሬዝዳንት፣ የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ሊቀመንበር፣ የኦሮሞ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ኢ-መደበኛ አፈቀላጤ።

ጃዋርን የሰባት ኪሎ ፊት ለፊት ተጋባዥ ላደርገው ስወስንም ይህን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያለውን ጉልህ ቦታ እና ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ባለፉት ሦስት ወራት ጃዋርን ሁለት ጊዜ በስልክ አግኝቼው ከአራት ሰዓት በላይ የቆየ ቃለ ምልልስ አድርጌያለሁ። የልጅነት ታሪኩም ይኹን የአሁኑ የፖለቲካ ተሳትፎው ለማወቅ ጉጉት የሚያጭር ነው። ከጃዋር ጋራ በብዙ ሐሳቦች አልስማማም። የእርሱ ፖለቲካ የእኔ ፖለቲካ አይደለም። የእርሱ እሴት የእኔ እሴት አይደለም፤ ይኹንና ሲያወራ እጅግ ቀልብ የሚስብ፣ ብዙ ያነበበ እና ያሰላሰለ፣ ለዓላማው ጽናት ያለው፣ ለተቀናቃኞች የሚያስቸግር፣ ለወዳጅም የቤት ሥራ የኾነ ሰው መኾኑን መካድ አይቻልም። በእነዚህ ሁለት ቃለ ምልልሶች፣ ጃዋር አንዳንዴ አስቆጥቶኛል፤ አንዳንዴ አስደምሞኛል፤ አንዳንዴ አስቆኛል። ሳልጠይቅ ያለፍኳቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ተጨማሪ **10** ሰዓት ቢሰጠኝ እንኳ የሚበቃኝ አይመስለኝም። ቃለ ምልልሱን ከድምጽ ወደ ጽሑፍ መልሼ ሳነበው **"**ወይኔ እዚህ ጋ ሸወደኝ**"** ያልኩባቸው በርካታ ቦታዎች አሉ። ጽሑፉን ያነበቡ የሰባት ኪሎ ጓዶቼ አንዱ **"**አረ ይኼ ሰውዬ ጭልጥ ብሎ የፍራንሲስ ፉኩያማ ተከታይ **(**ፉኩያሚስት**)** ኾነ**"** ሲል፣ ሌላው **"**እንዴ ሰውየው ኤድመንድ በርክን መመጥመጥ ጀመረ እንዴ**"** ሲል ሌላው ደግሞ **"**አቤት ወገብ፣ አቤት መተጣጠፍ**"** ሲል ፈገግ አሰኘኝ፤ ከጥያቄዎቼ አንዱ **"**መለስን ትመስላለህ**?"** የሚል ስለነበር። አንባቢዎቼ፡- ይኼን ቃለ ምልልስ ኮምኩማችሁ ስለ ጃዋር ከሰባት ኪሎ ጓዶቼ የተሻለ የተጨበጠ መረጃ እንደምታገኙ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ይኸው **. . . .**

**(**ዳኘነት መኮንን**)**

## <u>ልጅነትና ፖለቲካ</u>

ስለተወለድክበት እና የልጅነት ዘመንህን ስላሳለፍክበት ስለ ድሙጋ ትንሽ አውጋኝ።

በርግጥ ድሙጋ ያደግኹበት እና ራሴን ያወቅኹበት ከተማ ነው፤ በቅርቡ እናቴ እዚህ መጥታ ስትነግረኝ፤ የተወለድኩት ቤተሰቦቼ ይኖሩበት ከነበረ ዲማ ከሚባል ስፍራ ነው፤ ሰኞ ገበያ የሚባል ቦታ ነው፤ ቤተሰቦቿ ጋር ሄዳ ወለደችኝ፤ ከዚያ በኋላ ወደ ድሙጋ መጣን፤ እና እዚያው አደግኹ። በአርሲ እና ሐረርጌ ድንበር አካባቢ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ነች፤ ድሮ የኦነግ ወታደራዊ ንቅናቄ ካምፕም በአካባቢው ነበር፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋ ቡና ነው፤ በጣም ብዙ ውኃ አለ በአካባቢው፤ ከደጋ አርሲ የሚመጡ ወደ **27** የሚኾኑ ወንዞች አሉ፤ ትልልቅ የመንግሥት የቡና እርሻዎች አሉ፤ የተለያየ ዐይነት እና ቅይጥ የኾነ ባህል የሚታይባት ከተማ ነች። ከኦሮሞ ጎሳዎች ውስጥ ከነምሳ ቀነንዴ የሚመጡት የአፈንቀሎ ጎሳዎች በብዛት አሉ፤ በአካባቢው ደግሞ የአርሲ እና የኢቱ ጎሳዎች አሉ፤ ከሰላሌ ከሸዋ የመጡ የእናቴ ዘመዶች እና ወደዛ ፈልሰው ያሉ አሉ፤ አማራዎች አሉ፤ ኤርትራውያን ሁሉ ያሉባት እና በብዙ ባህሎች ስብጥር የተዋበች ከተማ ነበረች – ያኔ እኔ ሳድግ።

ድሙጋ እስከ ስንተኛ ክፍል ተማርክ**?**

ድሙጋ ሰባት ጨርሼ ወደ ስምንት ስሻገር ወደ አሰላ ተዛወርኩ፤ ከዚያ በኋላ አሰላ ሁለት ዓመት ተማርኩ። ስምንተኛ ክፍል እያለሁ ከትምህርት ቤት ተባርሬ ነበር።

በምን ተባረርክ**?**

የፖለቲካ ሱስ ነዋ፤ እዚያ እያለሁ ሰልፍ አስወጣኹባቸው፤ በእነዚሁ ሰዎች ላይ፤ እዚያ እያለሁ የኾነ እንዲሁ ዐይነት እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር። በማሳደሜ ምክንያት ስምንተኛ ክፍልን እንዳለ ዘግተው ሁላችንንም ከትምህርት ቤት አባረሩን። የተዘጋው ታህሳስ ወር ላይ ይመስለኛል፤ ከዚያ እኔ ወደ አሳላ መጣሁና መማር ጀመርኩ።

ይህ የመጀመርያው የፖለቲካ ተቃውሞህ ነው**?**

ለመጀመርያ ጊዜ ተማሪዎችን አሰልፌ ፖሊስ ጣቢያ የተወሰድኹት የስድስተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ነበር። ስምንተኛ ክፍል ላይ ስደርስ አንድ የኦሕዴድ የምሥረታ በዐል ነበር፤ በዚያ በዐል ላይ እኛ የኦነግን መዝሙር ዘመርን። እና በዚያው ተባረርን፤ ይኼ እንግዲህ በ **1992/3** ዓ**.**ም መኾኑ ነው።

የአሰላ ቆይታህ እና የፖለቲካ ተሳትፎህስ ምን ይመስል ነበር**?** ስለ አሰላስ የሚሰማህ ምንድን ነው**?**

ድሙጋ ማለት ትንሿ ድሬዳዋ ማለት ናት፤ ብዙ ዐይነት ሰው ያለባት፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋ የተጋጋለ፤ አኗኗሩም ሞቅ ያለ ነው። አሰላ ስትመጣ በተቃራኒው ቀዝቃዛ ነው፤ አሰላም እንደ ድሙጋ የባልህ ስብጥር የሚታይበት ከተማ ነው። ይኹን እንጂ ማኅበረሰቡ ወግ አጥባቂ ነው፤ እኛ ደግሞ ስንናገር ምላሳችን ለቀቅ ለቀቅ ይላል፤ በአኗኗሩ ደግሞ ሰብሰብ ብለህ በጨዋ መኖር አለብህ፤ ከዚያ ጋራ መዋሃድ መጀመርያ ላይ ስደርስ ፈተና ኾኖብኝ ነበር። እኛ ጋ እንግዲህ **'**እርስዎ**'** የሚባል ነገር የለም፤ አንቱ የሚባል ነገር የለም፤ ማንም ይኹን ማን ሁሉም አንተ ነው፤ እና አንድ ጊዜ ክፍል ውስጥ የሂሳብ አስተማሪ ሂሳብ እየሠራ እያለ የስሌት ስህተት ይፈጥራል፤ **"**ቲቸር እዚያ ጋ ተሳስተኻል፤**"**አልኩት። ዞሮ **"**ማንን ነው የምትለው**?** ከዚህ ከእኔ ጀርባ ሌላ ሰው አለ እንዴ**?"** እያለ ይጠይቀኛል። ከዚያ እኔ **"**አንተን እኮ ነው የምልህ**"** ስለው ጆሮዬን ይዞ ዳይሬክተሩ ጋ ወሰደኝ። ከዚያ ዳይሬክተሩ **"**በምን ተጣላችሁ**?"** ብሎ ሲጠይቀኝ **"**እኔ ምን አውቃለሁ **. . .** ሂሳብ ስሌት ላይ ተሳስተኻል ስለው**"** ብዬ ሳልጨርስ ዳይሬክተሩ በሳቅ ሞተ። ዳይሬክተሩ አረማ ስለተማረ ባደግኹበት ባህል ውስጥ አንቱታ እንደሌለ ያውቃል። ከዚያ በኋላ አንቱ ለሚለው ምላሴን ወፈር ማድረግ ጀመርኩ፤ እርሱ አንዱ ተግዳሮት ነበር። ስምንተኛ ክፍል ካቶሊክ ትምህርት ቤት ነው የተማርኹት፤ ከዚያ በፊት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት እማር ነበር፤ ከእናቴ ቤተሰቦች እና ዘመዶች ጋራ፤ ለእኔ በጣም ደስ የሚል እና ለየት ያለ ጊዜ ነበር ያኔ። በአጠቃላይ ስምንተኛ ክፍል የነበረኝ ጊዜ ደስ የሚል ነበር። ዘጠነኛ ክፍል እንደገባሁ ደብቄ የተቀመጥኹት ፖለቲካ እንደገና አገረሸብኝ፤ ማደራጀት ጀመርን፤ የምማርበት ትምህርት ቤት ጭላሎ ነበር፤ ፖለቲካው ሳይጀመር የተማሪዎች ክበብ በሚባለው ውስጥ መሳተፍ ጀምሬ ነበር፤ በማኅበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎችን ማነቃቃት እና ማደራጀት ላይ ተሳትፎ አደርግ ነበር፤ ከዚያ በባሌ ደን ጉዳይ ላይ ተቃውሞ እንዲሰማ አደረግን፤ ትልቅ ሰልፍ ተደረገ፤ እዚያ ያሉት የአስተዳደር አካላት ማስጠንቀቂያ ሰጡኝ፤ ሲረዱኝ የነበሩ ሰዎች **"**አሁንም ከዚህ ከተባረርክ አስቸጋሪ ነው የሚኾነው፤ ስለዚህ ትምህርት ቤቱን ልቀቅ እና ወደ አዳማ ሂድ**"** ተባልኩ፤ አዳማ ሄድኩ እዚያ **10**ኛ ክፍል ገባሁ፤ ዐሥረኛ ጨርሼ ወደ ዐሥራ አንደኛ እንዳለፍኩ ነው ወደ ሲንጋፖር የመጣሁት። አዳማም በጣም በተማሪዎች እንቅስቃሴ፣ በአጠቃላይ በምሥራቅ ሸዋ፣ በምዕራብ ሐረርጌ እና በአርሲ አካባቢ በውስጥ በመንቀሳቀስ አደራጅ ነበር፤ በፖለቲካ ብቻ ሳይኾን በባህል ጉዳይ ላይ፣ መሠረተ ትምህርት በማስፋፋት

ጉዳዮች ላይ እሳተፍ ነበር፤ አዳማ እያለሁ። በስፋት አክቲቪስ የነበርኹት አዳማ ነው ማለት ይቻላል።

## ጃዋር በእስያ፤ ባህል እና ፖለቲካ

ወደ ሲንጋፖር የሚያስጉዝህን ስኮላርሺፕ እንዴት አገኘህ? የሲንጋፖር ቆይታህስ እንዴት ነበር?

ዩናይትድ ዎርልድ ኮሌጅ የሚባል የትምህርት ተቋም አለ። ያኔ እኔ ስሄድ ዐሥር ትምህርት ቤቶች ነበሩት፤ ይኼው ኮሌጅ ከየአገሩ ተማሪዎችን እያመጣ ያስተምራል፤ እንደ 'ፕሪፓራቶሪ' ዐይነት ነገር ነው፤ **11**ኛ እና **12**ኛ ክፍል ያስተምራሉ፤ ግን ተጨማሪ አድቫንስድ ኮርስም ይሰጣል፤ **10**ኛ ክፍል ጨርሰው ጥሩ ነጥብ ያላቸውን ልጆች እና በትምህርት ቤት ውስጥም በአመራር ደረጃ አክቲቭ ከኾኑ ተማሪዎች ውስጥ አንድ አንድ ተማሪ ዕጩ አድርጋችሁ አቅርቡ ይባላሉ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች፤ ዳይሬክተሩ እና መምህራን ዕጩ አድርገው ያቀርቡኻል፤ ከዚያ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች የተሰባሰቡ ተማሪዎች ተወዳድረው ይጣራ እና የመጨረሻዎቹ **25** ተጠራን። ይኼን ዩናይትድ ዎርልድ ኮሌጅ እነ ሪቻርድ ፓንክረስት እና ሪታ ፓንክረስት የሚያስተዳድሩት ነው፤ አዲስ አበባ ውስጥ የሚታወቅ ድርጅት ነው፤ **25**ቱ ተማሪዎች ለኢንተርቪው ቀረብን፤ የጽሑፍ ፈተና ነበር፤ እኔ ፈጽሞ የማልፍ አልመሰለኝም ነበር፤ እንግሊዝኛ አልችልም ነበር፤ ሌሎቹ ተማሪዎች እንግሊዝኛውን እንደውኃ ያንቆረቁሩታል፤ ማታ ላይ አልፈኻል ተብሎ ሲነገረኝ ደነገጥኹ። ቀን ላይ ከቃለ ምልልሱ እና ከጽሑፍ ፈተናው ውጪ አንደኛው መስፈርት አገር መምረጥ ነበር፤ አሜሪካ፣ ኢንግላድ፣ ጣልያን፣ ኖርዌይ እና ካናዳ **. . .** እኔ ግን ከአንድ እስከ ሰባት ካሉት አማራጮች ዐይቼ መጨረሻ ላይ ያለውን ሲንጋፖርን መረጥኹ።

ለምን?

ዐየህ **. . .** ድሙጋ እያለሁ እንግሊዝኛ ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ፤ በጊዜው ምንም ዐይነት የእንግሊዝኛ ጋዜጣ አልነበረም፤ ዕቃ የሚጠቀለልበት ጋዜጣ ብቻ ነበር፤ ስትሬት ታይምስ የሚባል ባለቀለም ጋዜጣ አግኝቼ ሳነብ ሲንጋፖር የሚል ዐየቼ ነበር። እኔ ሲንጋፖር በዚያ ሰዓት ኤዥያ ውስጥ ያለች መኾኗን አላውቅም ነበር፤ አውሮፓ ውስጥ ያለች ከተማ ናት ብዬ አስብ ነበር፤ ከዚያ ሲንጋፖርን ካርታ ላይ ማፈላለግ ጀመርኩ፤ በዚያ ወቅት ሳርስ የሚባል በሽታ ተነስቶ ነበር፤ የሚያውቁኝ ሰዎች **"**የወፍ በሽታ ያለበት አገር አትሄድም፤ ለመሞት**"** አሉኝ። ይኹን እንጂ ከሲንጋፖር ጉዞ አልቀረኹም፤ ሲንጋፖር ሄጄ ሁለት ዓመት ተማርኩ።

የባህል ልዩነቱ ድንጋጤ ምን ይመስል ነበር?

ከብዙ አገራት የመጣን **17** ተማሪዎች ነበርን። የባህል ልዩነቱ እጅግ ሰፊ ነበር፤ ከዚያ በተጨማሪ የአገሩ ሰው ከእኛ ጋራ አይማርም፤ አስተማሪዎች ደግሞ አብረውን አይኖሩም፤ በዚህም የተነሳ ደንጋጤው ከባድ ነበር፤ ትምህርቱ በጣም ከፍ ያለ እና ደረጃውን የጠበቀ ነበር፤ የቀለም ትምህርት ብቻ ሳይኾን ተግባራዊ ትምህርትም እንማራለን፤ በተለይ ስለ ባህል 'ሴንሲቲቪቲ'፣ ስለ ባህል ግጭት ማኔጅመንት፣ ብዙ ነገር ትማራለህ፤ ጥሩ የለውጥ ጊዜ ነበር፤ በዚያ ላይ የራስህን ቋንቋ መማር ይፈቀድልኻል፤ እንዲያውም እሱን የበለጠ እንድታዳብረው ትበረታታለህ፤ እኔ እዚያ አፋን ኦሮሞን ነበር የተማርኩት፤ ለመጀመርያ ጊዜ አፋን ኦሮሞ የተማርኩት እኔ ነኝ፤ ያም በራሱ የሚያጓጓ እና የሚመስጥ ተግዳሮት ነበር። ያኔ ዓለማቀፍ አክቲቪዝም ውስጥ፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ውስጥ **(**ለምሳሌ የሲሪላንካን ግጭት በመሸምገል**)**፣ የወጣቶች ተነሳሽነት ውስጥ እሳተፍ ነበር፤ ወደ ቤልጂየም ሄጄ'ክላሽ ኦፍ ሲቪላይዜሽን'ዐይነት በስደተኛው እና በነባሩ መካከል ያለውን ግጭት የማጥራት እና የመሸምገል እና ኮንፈረንስ የማዘጋጀት ዕድል ነበረኝ፤ እንዲሁም ካናዳ በስረ-ቀዬ **(indigenous)** ሕዝብ እና በሌላው ማኅበረሰብ መካከል ያለውን **. . .** በተለያዩ አገሮች በካምቦዲያ፣ በላዖስ፣ እና በሌሎችም አገሮች በብዛት ተጉዤ ነበር፤ ያ ወቅት ለእኔ በጣም የለውጥ የሚባል ጊዜ ነበር። ወደ ብዙ አገሮች እሄድ ነበር፡ ማሌዢያ እዚያው በር ላይ ስለኾነ በየሁለት ሳምንቱ እሄድ ነበር፤ ታይላንድ እንሄዳለን፤ ሕንድ እና ኔፓል ጭምር እሄድ ነበር፤ ከዚያ ውጪ አውሮፓ ኔዘርላንድስ ለኮንፈራንስ ሄጄ ነበር፤ ካናዳም እንዲሁ። የወጣቶች ተነሳሽነት አስባባሪ ኾኜ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ሄጄ ነበር፤ ኤዥያ ውስጥ ግን የቀረኝ አገር ያለ አይመስለኝም።

ብዙ ጊዜ ስንጓዝ "መንገድ ላይ ያለሁት፤ ወደ ቤቴ ስለምመለስ ነው" በሚል መንፈስ ነው። ቤት ብዙ ጊዜ ማጣቀሻ ነጥብ (ሪፈረንስ ፖይንት) እና መስታወት ነው፤ በጉርምስናህ ከአገር ወደ አገር ስትጓዝ አንተ ውስጥ ከቀረው የአገር ቤት ማንነት፣ ባህል እና ፖለቲካ ጋራ እያነጻጸርክ እና እያወዳደርክ ትለካ ነበር?

ከባህል አንጻር ስታየው፤ በተለይ እኔ ካደግኹበት ጋራ እና በአጠቃላይ ኢትዮጵያን የሚቀርበው ማሌዢያ ነው ማለት ይቻላል፤ እስከ አሁንም ድረስ ባላገር (ኢንዲጂኒየስ) ናቸው፤ በርግጥ ቅኝ ተይዘው ነበር፤ ነገር ግን የነበረው የቅኝ አገዛዝ የደች ዐይነት ቅኝ አገዛዝ ነው፤ በኋላ ላይ የእንግሊዞች በተወሰነ ደረጃ።

መሳይ ከበደ 'ካልቸራል ዲስሎኬሽን' የሚለው ችግር ያልተንሰራፋበት ሞደርኒቲ አላቸው?

ብዙ የባህል ጥፋት አይታይበትም። የሕዝቡ አስተሳሰብ እና የማኅበራዊ ሕይወቱ እኩልነትን ያማከለ (ኢጋሊቴሪያን) ነው፤ በጎሳ የተያያዘ ነው፤ ሰው ይረዳዳል፤ የተለየ ነው። እኔ ባደግኹበት ከትምህርት ቤት ስትመጣ ምሳህን የትኛውም ሰው ቤት ውስጥ ትበላለህ፤ ማሌዢያ እንደዚያ ዐይነት ነገር ታያለህ። ወደ ችግሩ ስትመጣ ደግሞ በተለይ ሲሪላንካ የብሔር ግጭቱን፣ ፖለቲካውን ስታየው ከእኛ አገር ጋር ይመሳሰላል፤ የዚያን ጊዜ ታሚል ታይገሮች ከጦርነት ወደ ሰላም የመጡበት አካባቢ ነው፤ ያኔ ነበር ኮንፈረንስ ያዘጋጀነው። የነበረውን ውጥረት በተወሰነ ደረጃም ቢኾን ታየዋለህ። እኔ ሳድግ ደግሞ በኦነግ እና በሕወሓት መካከል ጦርነት ስለነበረ፤ ያንን ታያለህ፤ ከኤዥያ በጣም ብዙ የምንማረው ነገር አለ፤ ሁሉም አገራት የተለያየ የእድገት መንገድ ተጠቅመው የሚሄዱት፤ ለምሳሌ፡- ታይላንድን እና ማሌዢያን ብታነጻጽራቸው ጎረቤታሞች ናቸው፤ የሚከተሉት የኢኮኖሚ መንገድ በጣም ይለያያል። የባህል ዕድገቱን ስትመለከተውም ልዩነት ይታያል፤ ታይላድ በኢኮኖሚ እድገት የጀመረችው አሜሪካ ቬትናምን በምትደበድብበት ወቅት ነበር፤ የዚያን ጊዜ የአሜሪካ ወታደር እንደ ቤዝ አድርጎ ይጠቅምባት ነበር። ያን ተጠቅመው ኢኮኖሚያቸው ማደግ ችሏል፤ ግን ባህላቸው ሙሉ ለሙሉ ነው የተደመሰሰው። መጥፎ መጥፎ የምዕራብ ባህል ገብቶ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ኢ-እኩልነት የሚታይበት ዕድገት የተፈጠረበት ኾኗል። በጣም የተበከለ ዐይነት ባህል ነው የምታየው ታይላንድ ውስጥ። ማሌዢያ ግን በጣም ግትር የኾኑ ብሔረተኛ መሪዎች ነበሯቸው፤ ከነጻነት በኋላ የመጡት። እነ ቱኩዋንደራህማን የሚባሉ፤ ቢያንስ በኤሊት ደረጃ ስምምነት ስለፈጠሩ የውጭውን ኩባንያ ተጽዕኖ ቀንሰው በብዛት በራሳቸው ችሎታ አደጉ፤ ባህሉ ባለበት ተጠብቆ ከዘመናዊነት ጋራ እየተብላላ የራሱን ዘመናዊነት እየፈጠረ ተራመደ። ኢምፖርትድ የኾነ ዘመናዊነት ሳይኾን፣ እዚያው የተፈጠረ እና ያደገ ዘመናዊነት ስለኾነ የባህል መናጋት አደጋን በጣም መገደብ ተችሏል። የኢኮኖሚ ዕድገቱን ኢኮኖሚስቶች እኩልነትን ለመለካት የሚጠቀሙበትን ጂኒ ኮፊሸንትን ብትመለከት ማሌዢያ ከታይላንድ በብዙ ይለያል። ታይላንድ ውስጥ የማይሸጥ ነገር የለም። ሰው ሲሸጥ ታያለህ፤ ይህ በማሌዢያ አይታሰብም።

እዚያው ጎረቤት ላዖስ የሚባል አገር ስትሄድ ደግሞ፤ እስከ አሁን ኮሚኒዝም ነው፤ እስከ አሁን የራሽያ መኪና ነው የሚነዱት፣ እስከ አሁን ድረስ ባንዲራ ሲወጣ እና ሲወርድ ዝግ ብለህ ካላቆምክ በጥፊ ትመታለህ። እዚያው ጋ ደግሞ ቬትናሞች በከፍተኛ የኢኮኖሚ ፍጥነት ሲሄዱ ታያለህ፤ እዚያው ጋ ደግሞ ማሌዢያ በተረጋጋ ፍጥነት ስተጓዝ ትመለከታለህ፣ እዚያ ጋ ደግሞ ታይላንድ ምስቅልቅሉ ወጥቷል፤ እዚህ ጋ ደግሞ ላዖስ የሚባል ልክ ይኼ . . ድሮ በሠርቶ አደር ጋዜጣ የምታያትን ዐይነት ኢትዮጵያ ታያለህ።

መለስ ዜናዊ ስለ ኤዢያ ሞዴል ብዙ ይናገር ነበር፡- አንድ እርሱ ያላገኘው እኔ በቅርብ ያስተዋልኩት ምን መሰለህ፡- የኤዢያ ሞዴል የሚባል ነገር የለም። ሁሉም አገሮች የየራሳቸው የኾነ ሞዴል ነበራቸው፤ ሁሉም አገሮች የየራሳቸው በጎና መጥፎ ነበራቸው፤ እኔ ያኔ ማሌዢያ ውስጥ በአውቶብስ እና በባቡር እያንዳንዱን ገጠር እየዞርኩ እመለከት ነበር፤ ገበሬ ቤት እያደርኩ። እና እንደ አገር ማድረግ ያለብህም ማድረግ የሌለብህም ብዙ ነገሮች ትማራለህ።

ስለሲሪላንካ ስታነሳ ከኢትዮጵያ ጋራ የሚመሳሰል የፖለቲካ ችግር እንዳላቸው አንስተሃል፤ አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ የሚመስሉ ችግሮች የተለያዩ መንስዔዎች አሏቸው። እስቲ ስለ መንስዔ እናውራ። የመንግሥት (ስቴት) ጭቆና እና ጭፍለቃ ከእኛ ጋር ይመሳሰላል። የብዙኀን እና ውህዳን ስብጥሩን እና የኀይል ሚዛኑን ከውጭ ሲመለከቱት ግን የብዙኀን አምባገነንነት ችግር ይመስላል።

እንግዲህ እዚያ አገር ያሉት ሁለት ዋና ዋና ብሔሮች ናቸው፤ ታሚል እና ሲንሃሊዝ የሚባሉ። ሲንሃሊዝ የሚባሉት ሰባ በመቶ የሚኾኑ ይመስለኛል፤ ታሚሎች **15** በመቶ ይኾናሉ፤ በሰሜን ምሥራቅ አካባቢ ነው የሚኖሩት። በኮሎኒያሊዝም ጊዜ እንግሊዞቹ ታሚል 'ማይኖሪቲ' ስለነበረ ሥልጣን ላይ አቆይተውት ነበር። እነርሱን ተጠቅመው ነው ብዙኀኑን ሲገዙ የነበሩት። ከሥልጣን ሲወርዱ ግን ሥልጣኑን 'ለማጆሪቲው' አስተላልፈው ነው የሄዱት። ወደ ሥልጣን የመጡት ደግሞ የታሚል ልዩ ጥቅም አለ ብለው ስለነበር ያንን ለመጨፍለቅ ስለፈለጉ ብዙ ርምጃዎችን ወስደዋል።

ወደ እኛ ስንመጣ ከማሌዥያ ጋር ላነጻጽርልህ፤ የማሌዢያን ቅድመ ቅኝ ግዛት ማኔጅመንት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የሲሪላንካ ታሚሎች ቅኝ አገዛዝ ጋራ ሥልጣናቸውን አጡ። ታሚሎች በዚያ ጊዜ ብዙ ስለተማሩ ሰፊውን ልዩነት ለማመጣጠን የሲንሃሊዝ ልሂቃን ታሚሎችን በመጨቆን ወደኋላ የማስቀረት ርምጃ መውሰድ አለብን አሉ፤ እና ቋንቋቸውን ከትምህርት እና ከአገልግሎት እንዲወጣ አደረጉት፤ ታሚሎች እንግሊዝኛ ስለሚናገሩ እና ሲናሊዞች ስለማይናገሩ እንግሊዝኛንም ጭምር ከለከሉ፤ ስለዚህ ታሚሎች የባህል ጭቆና፣ የቋንቋ ጭቆና እና ኢኮኖሚያዊ መገለል ደረሰባቸው። ይኼ እንግዲህ በ **1960** ዎቹ በደንብ እየተብላላ የመጣ ነው። የታሚል ፓርቲዎች ልክ እኛ ጋ እንደሚታየው በሰላም እየሞከሩ አልኾነላቸውም፤ እያለ እያለ ወደ ጦርነት ሄዱ። የማሌዢያን ስንወስድ ደግሞ የቻይና ሰፋሪዎች **(**እንግሊዞች ያመጡዋቸው የቻይና የጉልበት ሠራተኞች ነበሩ**)** ብዛታቸው **10** ፐርሰንት ያህል ነው፤ ከእንግሊዞች ጋራ የቅኝ ግዛት ወኪል በመኾን የኢኮኖሚ አውታሩን ተቆጣጠሩት። እንግሊዞች እነርሱን ከማላዮች ጋር ለማጋጨት ሞክረው ነበር፤ የማሌዢያ ብሔረተኞች ግን የቻይናውያን ተጽዕኖ እንዲቀጥል አደረጉ። ያንን የበላይነት ለመስበር በሚያደርጉት ጥረት ምክንያት ጦርነት ውስጥ መግባት ስላልፈለጉ ቱንኩ የሚባለው ሰውዬ "ኢንላርጂንግ ዘ ፓይ" ቲዎሪ ይዞ መጣ።

እንግሊዞች የነበራቸው ሀብት እንዳለ ይወረስና ለማሌዢያውያን እንዲተላለፍ ይደረጋል፤ የቻይኒዞቹ እንዳለ አይነካም፤ ኢኮኖሚው በሚያድግበት ጊዜ የቻይኖቹ እንዳለ እየቀጠለ የማላዮቹ ግን በስፋት ማደግ አለበት፤ ቻይናዎቹ ምንም የሚያጡት ነገር የለም፤ ይህ ሁሉ ሲኾን የቻይኒስት ኮሚኒስት ፓርቲ እንቅስቃሴ ነበር፤ እነሱም ቡኖ የሚባል ፓርቲ ፈጠሩ፤ ቻይና በዚህ መልክ ጣልቃ ትገባ ነበር፤ ይሁንና ያንን ሁሉ መቆጣጠር ችለዋል። ሲሪላንካ ውስጥ ያንን ማድረግ አልቻሉም፤ ውጥረቱ በጣም እያየለ የታሚል ብሔረተኛነት እያደገ በመጣ ቁጥር እርሱን ለመስበር ያላደረጉት ነገር የለም፤ በተለይ የሰላማዊ ፖለቲካ ምህዳሩን በዘጉት ቁጥር፣ ባህሉ እንዳያድግ መንገዱን እየዘጉት በሄዱ ቁጥር፣ እየጠነከ እየጠነከረ መጣና ፓራብካሃራን  የተባለ አንድ ጎረምሳ (ያኔ 19